# እህቴ

ጠመዝማዛውን የኑሮ ጎዳና ደግፋ ያሳለፈችኝ፤
ፍቅርና አንድነት ውጤቱ ያማረ መሆኑን ያሳወቀችኝ፤
አብሮ አደግ ጓደኛዬ ነች የማትሰለቸኝ::

ንግግሯና ተግባሯ እጅግ ይመሳሰላል፤
ለጊዜው ተደሰት ብላ አትለኝም የማይሆነውን ይሆናል::

ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ አይዞሽ በርቺ እያለች፤
እቅፍ ሳም አድርጋ እያበረታታች፤
ቀኝ እጄን አለኝታዬ ሁሌም አጠገቤ አለች::

ሰው ከራሱ አብልጦ ይወዳል እንዴ ሰውን?
ወይኔ እናንተ ሰዎች ባያችሁ ይህች ሰው ለኔ የምትሆውን::

የደስታዬም ጊዜ የምትደሰት አብራኝ፤
የምትለኝ እሰይ የኔ ጎበዝ በጣም አኮራሽኝ፤
የሕሊና እረፍቴ ድጋፌ አለችልኝ::

እንደማር የጣፈጠ እንደወተት የነፃ ፍቅር ያላት፤
አስተማሪዬም ዘመዴም ጓደኛዬም እህቴ እኮ ናት::

ከ ኒኒ ለገሰ